# ምዕራፍ 1 – ማጠቃለያ

## መነሻ

ይህ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ (PPP) የተዘጋጀው የዋሽንግተን አካባቢ የጉዞ ባለሥልጣንን (WMATA) የስምሪት ፕሮግራም ለማስፋፋት፣ ከደንበኞች ጋር የሁለት መስመር ውይይት ለመደገፍ፣ የደንበኞችን ጥናት ምላሽ ለሚሟላት፣ ከደንበኞች ውጭ የሆነ አስተያየት በውሳኔ ውስጥ ለማካተት እና "በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ማንም ሰው በዘር፣ በቀለም ወይም በብሔር ምክንያት ማንኛውንም የፌደራል የገንዘብ እርዳታ መነፈግ፣ ጥቅማጥቅሞችን መከልከል ወይም አድልዎ መደረግ የለበትም"[1] የሚለውን በአንቀጽ 6 የተካተተውን የ1964 የሕዝብ መብቶች ድንጋጌ ለማሟላት ነው። በፌደራል መመሪያ መሠረት WMATA በዕቅዱ እና በፕሮግራም እንቅስቃሴዎቹ በቁጥር አነስተኛ የሆኑ እና ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችን (LEP) የሚያካትት የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ እና ዘዴዎች ለፌደራል ትራንስፖርት አስተዳደር (FTA) መስጠት አለበት።

*እነኝህ ጥረቶች ሌሎች በአኩልነት ያልተገለገሉ ክፍሎችን እንደ የአካል ጉዳት ያለባቸውን እና አነስተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎችን ጨምሮ ሰፋ ያሉ አቋሞች ክፍል ሊሆኑ ይችላሉ።*

የፌደራል ትራንስፖርት አስተዳደር (FTA) የፌደራል ገንዘብ ተጠቃሚ እንደመሆኑ እና በ1964 የህዝብ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 6 እና አፈጻጸም ድንጋጌዎች[2] መሠረት የፌደራል ትራንስፖርት አስተዳደር (FTA WMATA የሚከተሉትን እንዲያደርግ መመሪያ ይሰጠዋል፤

- የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ደረጃ እና ጥራት አድሎ በሌለው መንገድ መስጠቱን ማረጋገጥ፣
- የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ውሳኔን በተመለከተ በዘር፣ በቀለም፣ ወይም በብሄር ሳይወሰን የተሟላ እና ትክክለኛ ተሳትፎን ማራመድ፣
- ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪ ለሆኑ ሰዎች አስፈላጊ የሆኑ ትራንስፖርት ነክ ፕሮግራሞችን ማግኘታቸውን ማረጋገጥ።[3]

የፌደራል ትራንስፖርት አስተዳደር (FTA) የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጭዎች በቁጥር አነስተኛ የሆኑትን እና ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችን ለማሳተፍ የሚጠቀሙባቸውን ዘዴዎች እና የስምሪቱን ተፈላጊ ውጤቶች የሚያሳይ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ እንዲያዘጋጁ ይጠይቃል። ይህ ዕቅድ ሰፋ ያለ ሌሎችንም በልምድ ተገቢውን አገልግሎት ያላገኙ ህብረተሰቦችን፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸውን እና የአካል ጉድለት ያለባቸውን ጨምሮ የሚያካትት ሰፋ ያለ የህዝብ ተሳትፎ ዘዴ አንደኛው ክፍል ሊሆን ይችላል።

በWMATA ፕሮግራሞች ከመሳተፍ የሚያግዷቸው በብዙ የሚቆጠሩ እክሎች እና ችግሮች ላላቸው ቡድኖች፣ በቁጥር አነስተኛ የሆኑ፣ የገቢ ምንጫቸው፣ ወይም የእንግሊዝኛ ቋንቋ የመናገር ችሎታ የሌላቸውን ቡድኖች ጨምሮ ለሁሉም የስምሪት ዘዴ በማውጣት እና በመጠቀም አገልግሎትን ማሻሻል።

---

[1] 42 USC Section 200d
[2] FTA C 4702.1B
[3] FTA C 4702.1B

የሕዝብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች በአንድ ወጥ ሁሉን ባካተተ መንገድ ለሁሉም ሰዎች እንዲደርስ ይዘጋጃል።

## ዕቅዱን ማውጣት

የWMATA የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ አንድ ዓመት የወሰደ፣ በተለያየ ደረጃ ሂደት እና አሁን የህዝብ ስምሪት እንቅስቃሴዎችን ከሚያካሂዱ ክፍሎች እና ቢሮዎች ከተውጣጡ እና ከተለያዩ ክፍሎች በተወከሉ ቡድኖች የተመራ ነበር። ሁሉንም ኤጀንሲዎች የሚያጠቃልል አራት የህዝብ ተሳትፎ መልዕክት ዓላማዎችን ያቀርባል፣ ሁሉን ያካተተ፣ ተባባሪ፣ ውጤታማ እና ጽኑ። የህዝብ ተሳትፎ ውጤት የሚለካው በእነኝህ ዓላማዎች ነው። ቁጥር 1 እነኝህን ዓላማዎች ያብራራል።

**ቁጥር 1 የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ (PPP) ዓላማዎች**

| | |
|---|---|
| **ሁሉን ያካተተ** | **በህዝብ ተሳትፎ ሂደት ለመሳተፍ ተፅእኖ ሊደረስባቸው የሚችሉትን፣ በተለመደ መንገድ ለመድረስ አስቸጋሪ የሆኑትን ጨምሮ፣ ሁሉንም ማህበረሰብ ባህልን በማይነኩ ዘዴዎች ሙሉ በሙሉ ማሳተፍ።** |
| **ተባባሪ** | **በዕቅዱ እና በፕሮጀክቱ እንቅስቃሴ ሂደት ከማህበረሰቡ ጋር በህብረት መሥራት።** |
| ውጤታማ | **ዕምነትን ለመገንባት የህዝብን አስተያየት ከውጤቶች ጋር ማያያዝ።** |
| **ጽኑ** | **በ PPP የታቀዱ መመሪያዎች በመላው በWMATA ውስጥ በሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ።** |

WMATA የሚያካሂዳቸው የህዝብ ተሳትፎ ዕቅዶችን የሚያንቀሳቅሱ የተለያዩ እቅዶች እና የፕሮግራም እንቅስቃሴዎች አሉት። እነኝህም የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፣ የዕቅድ ፕሮጀክቶች፣ የፋሲሊቲዎች እና ተቋማት ምርጫዎች፣ የአካባቢ ጥናት፣ የአገልግሎት ለውጦች፣ የህዝብ መረጃ ዘመቻዎች እና የፖሊሲ አማራጮች - እንደ የክፍያ ለውጦች። የህዝብ ተሳትፎ ዕቅዱ በድርጊቱ ተጽእኖ የሚኖራቸውን ቡድኖች የተለያዩ አመለካከቶች እና ትኩረቶች አስፈላጊነቱን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለእነዚህ ዓይነት ፕሮጀክቶች ዘዴዎች ለማውጣት የተነደፈ ነበር።

የህዝብ ተሳትፎ ዕቅዶች ሂደት በዚህ አካባቢ ምርጥ ልምዶች ያሳዩ ኢንዱስትሪዎችን እንዲሁም በተለይ በWMATA አካባቢ የስምሪት እና የማሳተፍ ምርጫዎችን ያጠቃለሉ አምስት ዋና እንቅስቃሴዎች አሉት። የWMATA ሠራተኞች እና የቦርድ ዓባላት ቃለ መጠይቆች በአሁኑ ጊዜ በኤጀንሲው ወስጥ ያሉትን የሕዝብ ተሳትፎዎች እና ለወደፊት የሚደረጉ የአሠራር ሀሳቦች አጠቃላይ ሂደት አቅርቧል። ቁጥር 2 እነኝህን እንቅስቃሴዎች ያጠቃልላል።

የፕሮጀክቱ ዋና ዓላማ በWMATA አገልግሎት አካባቢ ለሚገኙ የተለያዩ ቡድኖች ስለመገናኛዎች እና የሕዝብ ተሳትፎ ምርጫዎች መረጃዎችን ለማግኘት የተደረገ ከፍተኛ እና አጠቃላይ ህዝብን የመድረስ ዘመቻ - *ሀሳብዎ ይናገሩ! የእርስዎ ጉዞ ነው* - ነበር። ተሳታፊዎቹ በቁጥር አነስተኛ የሆኑ፣ ስደተኞችን እና ጎሳዎችን፣ አካለ ጉዳተኞችን፣ አዛውንቶችን፣ ቤት አልባዎችን እና ችግረኞችን ያካትታል።

**ቁጥር 2 የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ (PPP) እድገት ሂደት**

**የፌደራል መስፈርቶች ግምገማ**

- አንቀጽ 6ን የተመለከቱ በሰነድ የተያዙ የሜትሮ የህዝብ ተሳትፎ መስፈርቶች። ይህ የFTA Circular 4701.2B እና ሌሎች የፌደራል መመሪያዎችን ጨምሮ ጥልቅ ግምገማን ያካትታል።.

**የተሻለ አሠራር ግምገማ**

- ከአስር መሰል የትራንስፖርት ኤጀንሲዎች ጋር የቴሌፎን መጠይቆች አድርጎ አጠቃላይ የህዝብ ተሳትፎ ዘዴዎቻቸውን ዝርዝር አስቀምጧል።

**የWMATA ሠራተኞች እና ቦርድ ዓባላቶች ቃለ መጠይቆች**

- አሁን ያሉት ሠራተኞች በህዝብ ተሳትፎ ያላቸውን ሚና እና የተሻለ የማህበረሰብ ተሳትፎን ለማወቅ ለ57 የሜትሮ ሠራተኞች እና አራት የሜትሮ ቦርድ ዓባሎች ቃለ መጠይቅ ተደርጓለ።

**የማህበረሰብ ድርጅቶች (CBO) ተሳትፎ**


- በWMATA አገልግሎት አካባቢ የሚሠሩ 87 የማህበረሰብ ድርጅቶች ስለተገልጋዮቻቸው የትራንስፖርት አጠቃቀም እና የመረጃ ምርጫዎቻቸው ቃለ መጠይቅ ተደርጓል።
- ከሰማንያ ሰባቱ ከዓርባ አንዱ የማህበረሰብ ድርጅት ከተመረጡ 15 ተወካዮች ጋር ጥልቅ የሆነ ውይይት ተደርጓል።

***ተናገሩ! የእርስዎ ጉዞ ነው ጥናት እና የስምሪት ዘመቻ***

- በWMATA አገልግሎት አካባቢ በሙሉ በተለያዩ 23 መንገዶች የስምሪት ዝግጅቶች ('በድንገት በመድረስ,' በማህበረሰብ ስብሰባ፣ ምርጥ ቡድን፣ በበዓል በመሳተፍ) ተካሂደዋል።
- ስለመረጃ ምርጫዎች ጥናት ከተሰበሰቡት 3,513 የህዝብ ምላሾች፣ 69% በቁጥር አነስተኞች፣ 28% አነስተኛ ገቢ ያላቸው፣ 10% ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ነበሩ።

ዘመቻው በሶስት ወራት፣ ከየካቲት እስከ ሚያዝያ 2014 ዓ.ም. ባለው ጊዜ ውስጥ በWMATA አገልግሎት መስጫ አካባቢዎች 38 የስምሪት ዝግጅቶችን አካሂዷል። ይህም ከ41 የማህበረሰብ ድርጅቶች (CBOs) የተውጣጡ 15 ጥልቅ የሆኑ የጥናት ቡድኖችን እና 23 በቁጥር እና በትኩረት የተለያዩ የህዝብ ስምሪት ዝግጅቶችን አካትቷል። ቁጥር 3 የሀያ ሶስቱን ይናገሩ! ቦታዎችን እና ዝግጅቶች ያሳያል፣ እንዲሁም የWMATA ሠራተኞች ከማህበረሰብ ድርጅቶች እና ተከታዮቻቸው ጋር የተገናኙበት 15 ጥልቅ የሆኑ የጥናት ቡድኖች ስብሰባዎችን ያሳያል።[4]

***ቁጥር 3 ይናገሩ! የእርስዎ ጉዞ ነው ዝግጅት የመድረስ ቦታዎች***




## *ይናገሩ! የእርስዎ ጉዞ ነው ጥናት*

ከተሳታፊዎች በየትኛው መንገድ ቢካፈሉ የተሻለ መሆኑን ለማወቅ ፕሮጀክቱ በሁሉም ዝግጅቶች እና በኦን ላይን ጥናቶች አካሂዷል። በአጠቃላይ ጥናቶቹ የተካሄዱት በታብሌት ኮምፒውተሮች ነበር፣ ሆኖም አንዳንዶቹ ቡድኖች በወረቀት ተጠቅመዋል፣ እንዲሁም ጥናቶቹ በWMATA አገልግሎት አካባቢዎች በሚነገሩባቸው ሰባት ዋና ዋና ቋንቋዎች ተተርጉመዋል። ባጠቃላይ *ይናገሩ! የእርስዎ ጉዞ ነው ጥናት*

[4] ይናገሩ! የእርስዎ ጉዞ ነው ጥናት እና የተኩረት ቡድን ስብሰባዎች በሁለት ቦታዎች ተካሂደዋል።

1,726 ጥናቶች ተካሂደዋል። ተጨማሪ 1,787 ጥናቶች በኦን ላይን ተካሂደዋል። መልስ ከሰጡት ተሳታፊዎች 69% በቁጥር አነስተኛ ከሆኑ ክፍል፣ 28% አነስተኛ ገቢ ያላቸው እና 10% ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ነበሩ።

በአጠቃላይ ከህዝብ እና ከማህበረሰብ ድርጅቶች የተሰበሰበው መረጃ የWMATA የህዝብ ስምሪት ጥረት ሁሉን ያካተተ እና ለሁሉም የሚደርስ መሆኑን ለማረጋገጥ ነበር። ይናገሩ! የእርስዎ ጉዞ ነው ዘመቻ ውጤቶች የሚከተሉትን ዕውቅና ሰጥተዋል።

- የማህበረሰብ ድርጅቶች ደንበኞቻቸውን/ተጠቃሚዎቻቸውን ለመድረስ የሚጠቀሙባቸውን ዘዴዎች፣ እና ከWMATA ጋር ለመተባበር ያላቸውን አስተያየት፣
- ከ3,513 ጥናት መልስ ሰጭዎች የተገኙ ግንኙነቶች እና ምርጫዎች፣ እና
- ለእያንዳድንዱ የስምሪት ዝግጅት ስለነበረውን ስኬቶች እና እክሎች።

የሚቀጥሉት ክፍሎች ከህዝብ እና ከመሰል ድርጅቶች፣ ከWMATA ሠራተኞች እና የቦርድ ዓባላት ቃለ መጠይቆች የተገኙትን ውጤቶች ይዘረዝራሉ።

## ቁልፍ ውጤቶች

### *የደንበኛ ምርጫዎች*

የተደረገው ሰፊ የስምሪት ጥረት በህዝቦች፣ በቁጥር አነስተኛ የሆኑ ክፍሎች፣ አነስተኛ ገቢ ያላችውን እና ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑትን ጨምሮ በWMATA የህዝብ ዝግጅቶች መሳተፍ ያላቸውን የሚከተሉትን የደንበኞች ምርጫዎች ጠቁሟል።

- *በአንቀጽ 6 የሚካተቱትን ህዝቦች ለማግኘት ወደ አሉበት ቦታ መሄድ። ከተሳተፉት* 10 በመቶ የሚሆኑት ግለሰቦች ብቻ በWMATA የህዝብ ስብሰባዎች አልተካፈሉም። በቁጥር አነስተኛ የሆኑ፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው እና ውስን የእንግሊዥኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በሚገኙበት ቦታ - በትራንስፖርት ማዕከሎች፣ በማህበረሰብ ድርጅቶች፣ በንግድ ማዕከሎች እና በዓሎች - የህዝብ ዝግጅቶች ማድረግ እነኝህን ክፍሎች ለመድረስ የበለጠ ውጤታማ ነው።
- *የባልህ ትኩርት መስጠት።* ተጠቃሚዎችን ማወቅ እና ተገቢውን የWMATA ሠራተኛ (በጉዳዩ፣ በባህሉ እና በቋንቋ ዕውቀት ያለው) ዝግጅቶች እና ስብሰባዎች ላይ ማሳተፍ።
- *ዝግጅቶችን ለመካፈል አመቺ ማድረግ።* በስብሰባዎች ለመካፈል አመቺ እንዲሆን ምን ማድረግ ይሻላል ተብሎ ሲጠየቁ፣ በሁሉም የዴሞግራፊ እና ባህል ክፍል ያሉ፣ ከውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በስተቀር የመጀመሪያ ሶስቱን አማራጮች መርጠዋል፣ ለሥራ ወይም ለቤት ቅርብ የሆነ ቦታ፣ በቀን አመቺ የሆነ ሰዓት፣ እና የህዝብ መጓጓዣ አቅራቢያ። ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች አመቺ ከሆነ ሰዓት ይልቅ አስተርጓሚ ማግኘትን መርጠዋል። ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች፣ የእስያ/ፓስፊክ አይላንደር ተወላጅ ተሳታፊዎች ከሥራ ቀን ይልቅ በሰንበት መሰብሰብ መፈለጋቸውን ገልጸዋል።
- *የዝግጅቱን ፎርማቶች አስተያየታቸውን ለማግኘት በሚፈለጉት ቡድኖች ፍላጎት ላይ ማትኮር።* የስብሰባዎች ፎርማቶች በእያንዳንዱ ቡድኖች ወይም ማህበረሰቦች ፍላጎቶች ላይ ማትኮር አለበት። ሁሉም ነጮች/ካውኬዥያን፣ እስፓኝ እና እስያ/ፓስፊክ አይላንደር ጥናት ተሳታፊዎች "የጥያቄ እና መልስ ጊዜያት" የስብሰባ ፎርማት የበለጠ እንደሚመርጡ አስታውቀዋል፣ ጥቁሮች/አፍሪካን አሜሪካን ተሳታፊዎች "እጅ በማውጣት መምረጥን" መርጠዋል። በዝግጅቶች ጊዜ በኤሌክትሮኒክ መምረጥ ለአዛውንቶች አመቺ አልነበረም። ሁሉም የዴሞግራፊ እና የባህል ቡድኖች ሰርቬይ፣ ክፍት ውይይት፣ እና የጥያቄ እና መልስ ክፍለ ጊዜዎች ከፍተኛ ምርጫቸው ነበሩ።

- *ሰነዶችን መተርጎም እና ሰዕሎች መጠቀም።* የመረጃ ሰነዶችን በተጠቃሚው ህዝብ ቋንቋ ማዘጋጀት እንዲሁም ሰዕሎች መጠቀም እና ጽሁፍ አለማብዛት ።
- *የብሄር ዜና ማሠራጫ እና የስርጭት ዘዴዎች መጠቀም።* ሰነዶች በብሄር/ዘር የዜና ማሰራጫዎች እና ተሳፋሪዎች በሚያዘወትሩበት አካባቢ፣ ባውቶቡስ (ጥቁሮች/አፍሪካን አሜሪካን፣ እስፓኞች፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው፣ እና ውስን የእንግሊዝዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚመርጡት)፣ ባውቶቡስ ማቆሚያዎች እና የባቡር ጣቢያዎች (ሁሉም ዘሮች፣ ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች እና አነስተኛ ገቢ ያላቸው ህዝቦች የሚመርጡት) አካባቢዎች መሰራጨት አለባቸው። ሰነዶች የመሳፈሪያ ቦታ ያልሆኑ እንደ የማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ቤተ መጻህፍት፣ የምግብ ሸቀጣሸቀጥ መደብሮች እና የመኖሪያ ቦታዎችም መበተን አለባቸው።
- *በጋዜጣ ማስታወቅ አሁንም ይሠራል።* ሁሉም ዘሮች፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው እና ውስን ቋንቋ ተናጋሪዎች መረጃዎችን ለማግኘት አብዛኛውን ጊዜ ጋዜጣ መጠቀም ይመርጣሉ፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸው እና ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪ መልስ ሰጭዎች ስለዝግጅቶች በኢንተርኔት መስማት በጣም ዝቅተኛ ነበር።
- *ለጆችን ጨምሩ።* ልጆችን የሚያካትቱ ዝግጅቶች ቤተሰቦች እንዲካፈሉ እና ትኩርት እንዲሰጡ ያደርጋል።
- *አስተያየት መቀበል እና መጠቀም።::* የህዝብ አስተዋጽዎ ውሳኔ በሚደረግበት ጊዜ እንዴት በጥቅም ላይ እንደሚውል ግልጽ መሆን አለበት።

## *መሰል፣ ሠራተኛ እና የቦርድ ቃለ መጠይቆች*

ከዚህ በታች የተጠቀሱት ከሠራተኞች እና የቦርድ ዓባላት ቃለ መጠይቆች የተሰጡ የተመረጡ አስተያየቶች እና የተሻለ አሠራር ልምዶች ግምገማዎች ናቸው፣

- *ዋና ክፍልን ያካተተ ድርጅታዊ መዋቅር ያለው የህዝብ ተሳትፎ መመሥረት።* በአጠቃላይ የህዝብ ተሳትፎ እንቅስቃሴን ብቻ የሚመለከት ክፍል እና/ወይም የበርካታ ክፍሎችን ተሳትፎ የሚያንቀሳቅስ ሂደት መኖር አለበት።
- *ከተለያዩ ህዝቦች ጋር ግንኙነቶች ለማድረግ እና እምነትን ለማትረፍ ከማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር መሥራት።* የማህበረሰብ ድርጅቶች ለትርፍ የማይሠሩ የአካባቢውን ማህበረሰብ የሚረዱ እና ለትራንስፖርት ኤጀንሲ አስፈላጊ የሆነውን የዘወተር እምነት እና ለሁለቱም ጠቃሚ የሆኑ ግንኙነቶችን ለመገንባት የሚረዱ ጠቃሚ ምኝጮች ናቸው። ሰፋ ያለ የህዝብ ተሳትፎ ለመገንባት እንዲረዳ ብዙዎቹ መሰል ኤጀንሲዎች የማህበረሰብ ድርጅቶች ኮሚቴዎች ፈጥረዋል።
- *ሰዎችን ባሉበት ማግኘት።* ተመሳሳይ ኤጀንሲዎች እና ሠራተኞች ተሳፋሪዎችን እና ሌሎች የህዝቡን ክፍል የኤጀንሲ ስብሰባዎችን እንዲካፍሉ ከመጠበቅ እና የተቻለውን ያህል ሁሉን ያካተተ የተሳትፎ እንቅስቃሴዎች ከማድረግ ይልቅ "ሰዎችን ባሉበት ማግኘት" የተሻለ መሆኑን ገልጸዋል።
- *መረጃውን ለማሠራጨት የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም።* በማህበረሰብ ድርጅቶች መረጃዎችን ማስተላለፍ በሁሉም ተቀባይነት ሲኖረው፣ ብዙ ድርጅቶች ሌሎች ዘዴዎችን፣ ለምሳሌ፣ መረጃዎችን ለቤተሰቦች ለማድረስ የተማሪዎች የሪፖርት ካርድ መስጫ ጊዜዎችን መጠቀም፣ በሚመለከታቸው አካባቢዎች ከቤት ወደ ቤት መሄድ፣ የብሄር የዜና ማሰራጫዎችን መጠቀም፣ ወዘተ… የ WMATA ሠራተኞች በቅርብ ባደረጓቸው የህዝብ ቅስቀሳዎች ከእነኝህ ቴክኒኮች አንዳንዶቹን በመጠቀም ውጤት አግኝተዋል፡፡
- *ቴክኖሎጂን በተገቢ መንገድ መጠቀም።* ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው ኤጀንሲዎች ለአብዛኛዎቹ ቴክኖሎጂ የራሱ ቦታ ሲኖረው ከሌሎች የስምሪት ሁኔታዎች ጋር መጠቀም እንዳለበት ስሜታቸውን ገልጸዋል። ቴክኖሎጂ በኦንላይን መጠይቆች፣ ዌቢናሮች፣ ወይም እንደ ማይንድሚክሰር ፕላትፎርሞች ጋር ጥቅም ላይ ሲውል ውጤታማ ነበር።
- *ተደጋጋሚ የህዝብ መድረኮች መጠቀም።* ህዝቡ ቅሬታ ባለው ጉዳዮች ላይ ለWMATA አስተያየት መስጠት እንዲችል ተደጋጋሚ መድረኮች ማዘጋጀት አስፈላጊነቱን ሠራተኞች ሃሳብ አቅርበዋል። ይህ አስተያየት አሁን ያሉ የተለዩ ፕሮጀክቶች፣ ፕሮፖሳሎች እና ዕቅዶች ላይ ሀሳብ የመስጠት ዕድሎችን ይደግፋል።

# አስተያየቶች

በFTA የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ አስፈላጊ ሁኔታዎች መሠረት፣ WMATA ከአነስተኛ ክፍል የሆኑትን፣ አነስተኛ ገቢ ያላቸውን እና ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ማህበረሰቦችን የሚያሳትፉ ተግባራዊ የሆኑ ዘዴዎችን ተገንዝቧል፣ ሁሉን የሚያካትት ሂደት እና የተለያዩ ሥርዓቶችን ፈጥሯል፣ እንዲሁም ኤጀንሲው የተፈለጉት ውጤቶች ግብ መምታታቸውን ለመከታተል የሚያስችሉ የአፈጻጸም መለኪያዎች አውጥቷል።

የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ የWMATA የህዝብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች ውጤታማ፣ የተቀላጠፉ እና የፌደራል ሁሉን ያቀፈ የህዝብ ተሳትፎ መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን የሚያረጋግጡ ዘዴዎችን ያጠቃልላል። እነዚህ ዘዴዎች የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ይዘት በተጀመረበት ጊዜ ከተሰበሰቡ መረጃዎች የተወሰዱ ናቸው። በህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ከሥልጣኑ የተወሰዱት የአሠራር ዘዴዎች በትክክል ሥራ ላይ መዋላቸውን ለFTA ለማረጋገጥ WMATA ተጠያቂ ይሆናል።

*ዘዴ 1: የህዝብ ተሳትፎ መሣሪያ እና የፕሮጀክት ግንኙነት/የስምሪት ዕቅድ*

ተናገሩ! የእርስዎ ጉዞ ነው ዘመቻ ጊዜ የተሰበሰበውን የደንበኞች ምርጫ፣ የሠራተኞች ቃለ መጠይቅ፣ እና የአቻ ኤጀንሲ ምርጥ አሠራሮችን በመጠቀም WMATA የፕሮጀክት ማኔጀሮች ውጤታማ የስምሪትት ዕቅድ እንዲያወጡ የሚረዳ መመሪያ አዘጋጅቷል። የመመሪያው ዋናው ትኩረት የፕሮጀክት ግንኙነቶች/የስምሪት ዕቅድ (PCOP) ነው። እያንዳንዱ የWMATA ፕሮጀክት የህዝብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎችን ለማቀድ PCOPን ይጠቀማል። PCOP ሠራተኞች ዝግጅቶችን፣ ቦታዎችን፣ የዜና ማሰራጫ እና ሌሎች ለተወሰነ ፕሮጀክት በውጤታማ መንገድ ተፈላጊውን ህዝብ ለመድረስ የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎችን ያጠቃልላል። መሣሪያው በተጨማሪ ለህዝቡ የተወሰነ የዜና ስምሪት ዝርዝሮች፣ የማህበረሰብ ድርጅቶች ዝርዝሮች እና አጠቃላይ ዓመታዊ ዝግጅቶች እና በWMATA አገልግሎት መስጫ አካባቢ የሚሰጡ ሌሎች ዝግጅቶችን ያካትታል።

WMATA የተለዩ ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን የተመለከቱ እና ሁሉን ያካተተ ጠቃሚ ተሳትፎ እንዲኖር ለማረጋገጥ እና ከWMATA እና ከማህበረሰብ ድርጅቶች አዲስ የዕውቀት መስመር ለመዘርጋት አካባቢው ከሚገኙ የማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ህብረት ይፈጥራል። የኮሚቴው ዓባልነት የአካባቢውን ከዳር እዳር ያሉትን የአገልግሎት ክፍሎች፣ በጂኦግራፊና የማህበረሰብ ድርጅቶችን ጨምሮ፣ ሁሉን ያጠቃለለ ይሆናል።

*ዘዴ 2: የአፈጻጸም መለኪያዎች*

ለእያንዳንዱ የህዝብ ተሳትፎ ፕሮጀክቶች፣ የተሳታፊዎች አስተያየቶች እና የተሳታፊዎች ክትትል ላይ የተመሠረቱ የአፈጻጸም መለኪያ ላይ ትኩረት የሚሰጡ መረጃዎች ይሰበሰባሉ። ዓመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርት ከግል ፕሮጀክት እና ዓመታዊ የማህበረሰብ ድርጅቶች የዳሰሳ ጥናት ወጤቶች የተሰበሰቡ መለኪያዎችን ያካትታሉ። ዓመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርት በዓመቱ ውስጥ የተደረጉ ውጤታማ የነበሩ አሠራሮችን ወይም ቦታዎችን መለየት እና ከተወሰደው ትምህርት ለወደፊት የስምሪት እንቅስቃሴዎችን አጠቃላይ ሀሳብ ይሰጣል።

*ዘዴ 3: የህዝብ ተሳትፌ ሥልጠና*

የመሣሪያውን ወጤታማ፣ አንድ ወጥ አጠቃቀም ለማረጋገጥ እና የአንቀጽ 6 መስፈርቶች የህዝብ ተሳትፎ በመላው በሥልጣኑ ግልጽ መሆኑን ለማረጋገጥ በስምሪቱ የተካፈሉ የWMATA ሠራተኖች መሣሪያውን እንዲጠቀሙ ይገደዳሉ እና ስለ መሣሪያው አጠቃቀም እና የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ሥልጠና ይወስዳሉ።

*ዘዴ 4: ማዕከላዊ የተሳትፎ ቢሮ*

ከመሳሪያው በተጨማሪ፣ የህዝብ ተሳትፎ ቢሮ የህዝብ ስምሪቶችን ለማስተዳደር WMATA ማዕከላዊ ቢሮ እንዲፈጥር አስተያየት ይሰጣል። የውጭ ጉዳዮች ግንኙነት ቢሮ (EREL) ለፕሮጀክት/ዕቅድ ሠራተኞች የግል ፕሮጀክቶች የባለሞያ እርዳታ የመስጠት ኃላፊነት ይኖረዋል። በተጨማሪም ቢሮው ሁሉንም በፕሮጀክት ላይ የተመሠረቱ የህዝብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም በWMATA ውስጥ የህዝብ ተሳትፎ ዕቅዶችን የማስተዳደር እና የማቀነባበር ኃላፊነት ይኖረዋል። EREL በመላው በድርጅቱ ውስጥ ጽኑነት፣ የግንኙነት እና የስምሪት ሰነዶች ጥራት መኖርን፣ ማስታወቂያዎችን በተመለከተ የማርኬቲንግ ቅንብር መኖርን እና የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል። በእኩልነት የመቀጠር ዕድል ቢሮ (OEEO)የማህበረሰብ ድርጅቶችን ከማስተዳደር እና የስምሪት ኃላፊነቶች ጋር የተያያዙ ተጨማሪ ሥራዎች ይኖረዋል።

## ማጠቃለያ

የWMATA የህዝብ ተሳትፎ ዕቅድ ግልጽ እና ግብ የሚመቱ ዓላማዎች ያሉት፣ የተፈተኑ የአካባቢ ዘዴዎች፣ ድርጅታዊ የውስጥ እና የአሠራር ዘዴዎች፣ እና ሁሉን ያካተቱ፣ ጽኑ፣ የህብረት እና ውጤታማ ምላሾችን የሚያካትት አጠቃላይ ሰነድ ነው። WMATA ይህንን ዕቅድ ሲያዘጋጅ የFTA ጥያቄዎችን ለማሟላት ብቻ ሳይሆን፣ በተራማጅ የህዝብ ተሳትፎ ጉዳዮች ላይ መሪ እንዲሆን ነው። በህዝብ ተሳትፎ ዕቅዶች

ላይ የተካተቱት PCOP እና መሣሪያዎች እና የአሠራር ዘዴዎች ሁሉን ያካተተ እና WMATA በሚያገለግለው፣ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ አቋም፣ በቁጥር አነስተኛ የሆኑ፣ ወይም ውስን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችን ጨምሮ፣ በሁሉም ህብረተሰብ ለሚገኙ ቡድኖች፣ በበለጠ የተቀላጠፈ እና ውጤታማ የህዝብ ተሳትፎ የሚያስከትል አጠቃላይ ሰነድ ነው።

*ሀሳብዎን ይናገሩ! የእርስዎ ጉዞ ነው ስምሪት ድንገተኛ ዝግጅት*

**በDC USA Mall**

